# ማን መሆን ይፈልጋሉ?

ተሳታፊዎች የመስመር ላይ ማንነታቸው እና የፈጠሩት እና ያጋሩት ይዘት ከግባቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ (ለምሳሌ ማከናወን የሚፈልጉዋቸው ስራ-ነክ፣ ኣካዳሚያዊ፣ ፍላጎቶች) ይገመግማሉ። ርእሰ-ጉዳይ፣ ፕላትፎርም፣ ስም፣ የታይታ ውክልና፣ እና የግላዊነት ቅንብሮች ከግምት ያስገባ የመስመር ላይ ማንነት እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል ይፈትሻሉ።

## ማቴርያሎች

የኦንላይን ማንነቴ የሚታደል ጽሑፍ

# የኦንላይን ማንነቴ

## ውይይት

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

አንድ ደቂቃ ሰጥተን ከተለያዩ ሰዎች ጋር እንደየማንነታቸው መስተጋብራችን እንዴት እንደሚሆን እናስብ። እርስዎ ከጓደኞችዎ ፊት ከቤተሰብ አባላቶችዎ ወይንም ትምህርት-ቤት ከሚገኙ አስተማሪዎችዎ በተለየ አቀራረብ መቅረብ ይችላሉ። በተጨማሪም እርስዎ እንደየቦታው ወይንም እንደየአጋጣሚው የተለየ አቀራረብ ሊከተሉ ይችላሉ — አንድ አቀራብ ትምህርት ቤት ላይ ከጓደኞችዎ ጋር ሲሆኑ፣ ከተመሳሳይ ጓደኞችዎ ጋር ከትምህርት-ቤት ውጪ ሲሆኑ ደግሞ ሌላ አቀራረብ።

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

ሁላችንም እንደምንገኝበት ቦታ እና አብሮን እንዳለ ሰው የተወሰነ ልዩነት እናሳያለን። ራስዎን እና ይዘትዎን ኦንላይን ላይ እንዴት ማቅረብ እንደሚፈልጉ የማስተዳደር ተመሳሳይ አቅም አሎት፣ ስለዚህ እርስዎ ኢንተርኔት ላይ ለሌሎች እንዴት ሆነው መቅረብ እንደሚፈልጉ ማሰብ መጀመርዎ ጥሩ ነው።

ዝነኛ ሰዎች (ለምሳሌ፣ ሙዚቃ እና / ወይንም ፊልም [ሙቪስ / ቲቪ] ኢንዳስትሪ ላይ የሚሰሩት፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ የንግድ ስራ መሪዎች) ሁልጊዜም ይህንን ያደርጋሉ። ከማህበራዊ ሚድያ ይዘት (ለምሳሌ፣ ምስሎች፣ ቪድዮዎች፣ ጽሑፍ ላይ የተመሰረቱ ልጥፎች) እስከ ቃለመጠይቆች፣ እያንዳንዱ የብራንዳቸው እና የህዝብ ፊት ህልውናቸው ክፍል በጥንቃቄ በመገንባት፣ በተቻለ መጠን ብዙ አድናቂዎቻቸው ወይንም ደንበኞች ለማጓጓት ይሞክራሉ።

የቢልዮን ዶላር የማርኬቲንግ ስትራቴጂ ያለው ዝነኛ ሰው መሆን አይጠበቅብዎትም። ይሁን እንጂ የእርስዎን የኦንላይን ህልውና ማን ሊያየው እንደሚችል ማሰብ እንዲሁም በመጪው ጊዜ ኦንላይን ላይ እንዴት መቅረብ እንዳብዎ ማቀድ ተቃሚ ነው።

## መስተጋብር

**የክላስ መስተጋብር** ተሳታፊዎችን በጥንድ ያደራጁ። ***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

በአሁኑ ጊዜ ምን አይነት ይዘት ያዘጋጃሉ / ወይንም ኦንላይን ላይ ያጋራሉ (ለምሳሌ፣ ቪድዮዎች፣ ሙዚቃ፣ ሪሚክሶች፣ ጦማሮች፣ ንድፎች፣ አኒመሽኖች)?

ይህንን ይዘት እንዲያዘጋጁ ወይንም እንዲያጋሩ ምን አነሳሳዎት? ለምንድነው ይህ የሚያደርጉት?

እውነተኛው ስምዎ እና ምስልዎ የሚገኝበት ይዘት ምን አይነት ነው?

በግልጽ ከእርስዎ ጋር እንዲተሳሰር የሚፈልጉት ይዘት ይኖራል? ለምን አልሆነም?

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎች እንዲወያዩ 7 ደቂቃ ይስጧቸው። ከዚያ ቡድኖቹ ሀሳቦቻቸውን እንዲያጋሩ ይጠይቁዋቸው።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

የመጪው ጊዜ የኦንላይን ህልውናዎ በተመለከተ ከመናገራችን በፊት፣ ስለ መጪው ጊዜ ግቦችዎ እንነጋገር። ከአጋርዎ ጋር ይወያዩ: ካደጉ በኋላ ማለትም በጥቂት አመታት ውስጥ የት እና ምን እንዲሆኑ ነው ይፈልጋሉ፣ እንዲሁም እንዴት ነው መጀመሪያ ይህ ሀሳብ ሊመጣልዎ የቻለው? በአሁኑ ጊዜ የሚመኙት ሀሳብ ወይንም ስራ ከአንድ በላይ ቢሆን ምንም ችግር የለውም።

ምን ከስራ ግብዎ(ቦችዎ) ያልተያያዙ ሌሎች ግላዊ ግቦች አንግበዋል?

የመጪ ጊዜ የስራ ግቦችዎ ወይንም የግል ግቦችዎ ለማሳካት ኦንላይን ላይ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

## የሚታደል ጽሁፍ

**የክላስ መስተጋብር**

የኦንላይን ማንነቴ የሚታደል ጽሑፍ ለተሳታፊዎች ያስተላልፉ። **ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው**

ኦንላይን ላይ የሚያደርጉት ነገር የአሁኑ ጊዜ ፍላጎቶችዎ ምን እንደሆኑ ለማግኘት እና የቀጣይ ጊዜ ጉጉቶችዎ ፈልገው እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

ይህንን የሚታደል ጽሑፍ ለመሙላት እና ራስዎን ኦንላይን ላይ በሚያቀርቡበት አውድ ውስጥ ጉግቶችዎ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ጥቂት ደቂቃዎች ወስደው ይግለጹ። የሁሉም ሰው የኦንላይን ማንነት የተለየ መሆኑ ልብ ይበሉ፣ የእርስዎ ማንነት ደግሞ የቀጣይ ጊዜ ግቦችዎ እና ፍላጎቶችዎ በተቀያየሩ ቁጥር እየተሻሻለ ይሄዳል።

# ምድብ ሥራ

## ምድብ ሥራ

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

አሁን እርስዎ ለራስዎ ያለዎት አመለካከት ምን እንደሚመስል እንዲሁም ፍላጎቶችዎን አይተናል፣ የማንነትዎ ሁኔታዎች ለሌሎች እንዴት ማሳየት እንደሚፈልጉ እናስብ።

የተወሰነ የማንነትዎ መገለጫ ላይ የሚያተኩር አዲስ የማህበራዊ ሚድያ ህልውና እየፈጠሩ ነው ብለን እናስብ። ከምንም ነው እየጀመሩ ያሉት እና ሁሉንም የግላዊነት ቅንብሮች የማስተካከል እንዲሁም ይዘትን በሚፈልጉት መልኩ የማቅረብ ሙሉ ነጻነት አሎት።

ይህንን አዲስ የማህበራዊ ሚድያ ህልውና እርስዎ የሚፈልጉት ገጽታ ለጓደኞችዎ እና ለተከታዮችዎ ለማስተላለፍ በሚመች መልኩ እንዴት ሊያዋቅሩት እንደሚችሉ በጽሑፍ ይግለጹ። በተለይ፣ የሚከተሉትን ንድፈ-ሀሳቦች ይናገሩ:

1. የመለያው እና የፕላትፎርሙ አይነት (ለምሳሌ፣ ማህበራዊ ሚድያ፣ ጦማር፣ ወዘተ)
2. የይዘቱ አይነት (ለምሳሌ፣ ቪድዮዎች፣ ጽሑፍ ላይ የተመሰረቱ ልጥፎች)
3. "ስለ እኔ" ክፍል ላይ ምን ማስቀመጥ ይፈልጋሉ?
4. ምን አይነት ስእሎችን ነው የሚጠቀሙት?
5. የግላዊነት ቅንብሮችዎ ምን ላይ ነው የሚያደርጉዋቸው? እነዚህ ቅንብሮቸ የሚያጋሩት ይዘት ላይ የተመሰረቱ ናቸው?

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።